# አንድ ከሚልዮን

አመሰግናለሁ፡ ወንድሜ። አመሰግናለው፡ ወንድም ሻካሪያን።

እንደምን አደራችሁ፡ ወዳጆቼ። በእርግጠኝነት ዛሬ ጠዋት ከዚህ ታላቅ ስብሰባ በፊትና በሚቀጥለው ሳምንት፡ ኤምባሲ ሆቴል ከሚካሄደው ሰብሰባ በፊት፡ እንደገና እዚህ ሎስ አንጀለስ በመገኘቴ በጣም ደስ ብሎኛል። ሁላችሁንም እዚያ ላያችሁ እጠብቃለሁ። ሁላችንም ከጌታችን ከኢየሱስ ጋር ለመገናኘት፡ እዚያ እሱን ለማየት በታላቅ ተስፋ ውስጥ ነን። እሱም ቃል ገብቶልናልና፡ “ሁለት ወይም ሦስት በሚሰበሰቡበት በመካከላቸው እገኛለሁ፡” ስለዚህ ይገኛል።

2 ዛሬም ጠዋት ሁሉም ሰዎች በታላቅ ጉጉት ቁርሳቸውን እና ሰብከቱን ሲጠብቁ፡ በዚህ አዳራሽ ደረጃዎች ላይ ሰወጣ፡ እርሱን እንዳገኘሁት እርግጠኛ ነኝ። እዚህም ከእናንተና ከሬዲዮ አድማጮች ጋር፡ መሰብሰብ በጣም ጥሩ ነገር ነው። እዚህ ውስጥ በጣም ብዙ ሰው አለ፡ ከ... ከጥቂቶች ጋር ለመነጋገር፡ ወደ ሚቀጥለው ፎቅ ወደ ታች መሄድ ነበረብኝ። ብዙ የጸሎት ጥያቄዎች፡ የልብ ሕመሞችንና፡ የተለያዩ የአካል ሕመሞችን አይተናል፡ አሁን ለታመሙ እና ለተጎዱት ለመጸለይ እዚህ ተገኝተናል።

3 ልክ ደረጃዎች ጫፍ ላይ ሰደርሰ... አሁን ሽማግሌ ሰው እየተመለከቱ ነው። ወደ እኔ ቀርቦ፡ እንዲህ አለኝ፡ “ወንድም ብራንሃም፡ ከዓመታት በፊት... ” የልብ ሕመም እንዳለበትና ሊ... ሊሞት ነው ብለው እንዳሰቡ ነገረኝ። ጸለይኩለት፡ የእግዚአብሔርም ጸጋ ፈወሰው። ዛሬም ጠዋት፡ በሰማንያዎቹ ዕድሜው፡ እየተደሰተ እዚህ ይገኛል። ስለዚህ ይህ አዲስ ተስፋ እንድናደርግ ያደርገናል።

4 አሁን በእርግጠኝነት በሬዲዮ ሰርጭት ውስጥ የሚከታተሉትን ሰዎች እንዲሁም እዚህ ያሉትን ሰዎች፡ ጸሎት እንዲታደርጉልኝ እጠይቃለሁ። ከዚህ ሰብሰባ ከወጣሁ በኋላ፡ ወደ አውሮፓ እሄዳለሁ፡ ወደ አፍሪካም እወርዳለሁ፡ ወደ ሰብሰባዎች እሄዳለሁ። ይህም የሚመራው በራእይ ነው፡ ስለዚህ እዚያ ታላቅ ሰብሰባ እንደሚሆን፡ እርግጠኛ ነኝ። ለዓመታት ጌታ ተመልሼ እንድመጣ እንደሚፈልግ ተሰምቶኛ ነበር። እርሱ ለእኔ የሰጠኝ፡ ትንሽ ትሕትና የተሞላበት አገልግሎት፡ እርሱ ገና፡ የበቃው አይመስለኝም። በወንጌል መረብ ውስጥ ልይዘው የምችለው ነፍስ የሆነ ቦታ ያለ ይመሰል ነበር፡ እርሱ ለሰዎች እንድይዝ የሰጠኝ፡ መለኮታዊ ፈውስ፡ ለታመሙ የመጸለይ መንገድ ነው። በእርግጠኝነት ጸሎታችሁን እጠይቃለሁ፡ እዚህ ያላችሁም፡ በሬዲዮ ሰርጭት የሚትከታተሉም ጸልዩልኝ።

5 በዚህ አዳራሽ ውሰጥ ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ፡ የ—የምጠብቀውን አንድ ጥቅሰ ወሰጄ ለ... ለመሰበክ ጊዜ የለኝም፡ ነገር ግን ለጥቂት ደቂቃዎች ለ—ለመተዋወቅ ያህል፡ እናገራለሁ። በአገሪቱ ውስጥ ላሉት ሰዎች፡ እዚያ ላሉት ሰዎች፡ ወዲያውኑ እጸልያለሁ፡ እዚህም እንዲሁ። ከዚህ በፊት ተገናኝቼ የማላውቃቸውን እነዚህን ሁሉ አዳዲሰ ጓደኞቼን በማግኘቴ በጣም ደሰ ብሎኛል፡ ልክ ዛሬ ጠዋት ነው ከእነሱ ጋር የተገናኘሁት።

6 በሌሎች ቦታዎች በሚካሄዱ አገልግሎቶች ጥሩ ጊዜ አሳልፈናል። ከአሁን በኋላ በጣም ብዙ አልወጣም፡ በጣም ቢዚ እሆናለሁና። በጄፈርሰንቪል፡ ኢንዲያና እና በቱክሰን፡ አሪዞና መካከል ያለውን መንገድ እየተመላለስንበት ነው፡ ወደዚያ የተዛወርነው ከጥቂት ዓመታት በፊት፡ በጌታ ራእይ ነው፡ ወዴት እንደምሄድ ሳላውቅ... ወደዚያ ላከኝ። ብዙዎቻችሁ እዚህ አላችሁ፡ በክሊፍተን፡ ከመሄዴ ትንሽ ቀደም ብዬ፡ በፎኒክስ ስብሰባ ላይ፡ ስለመጣው ራእይ ተናግሬ ነበር። ሰባት መላእክትን በቡድን አየሁ።

7 ለሬዲዮ ተመልካቾች፡ ይህ ትንሽ ምስጢራዊ እንደሚመስል፡ አውቃለሁ፡ ምናልባት ብዙዎቻችሁ ሙሉ ወንጌል አይደላችሁምና። በእናንተ ቦታ ቢሆን፡ ለእኔም ምስጥር ይሆን ነበር፡ ነገር ግን... ማንኛውንም ነገር አንድ ሰው ማብራራት የሚችል ከሆነ፡ ከእንግዲህ በእምነት መቀበል የለባችሁም። በእምነት መቀበል ያለብን፡ ማብራራት የማንችላቸው ነገሮች ናቸው። እግዚአብሔርን ልናብራራው አንችልም። እግዚአብሔርን ማንም ሰው ሊያብራራው አይችልም። ሉዓላዊ ነው፡ ታላቅና ኃያል ነው። የእርሱ መ—መኖር ስለምናውቅ ብቻ እንቀበላዋለን። ከዚያም በእምነታችን፡ በመቀበል፡ የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት፡ መልሱን መልሶ ያመጣልናል።

8 ይህም፡ ከትንሽ ጊዜ በኋላ፡ "የእግዚአብሔር" አሰራር፡ ወይም፡ "የአምልኮ ቦታ፡" በሚል ርዕስ፡ እናገራለሁ። እና እሱን ማምለክ የምትችሉበት ብቸኛው ቦታ፡ እሱ የሚያገኛችሁ ልዩ ቦታ... አለ፡ እግዚአብሔር በሚገናኝበት ነገር ሁሉ፡ አንድ ቤተክርስቲያን፡ አንድ ቦታ፡ አንድ ጊዜ፡ አንድ ሕዝብ አለ። ጌታም መልዕክቱን ለልባችሁ እንደሚባርክ ተሰፋ አደርጋለሁ።

9 አሁን፡ ወደ ቱክሰን መምጣት፡ እነዚህ ራዕዮች በጌታ ስም ሲነግራችሁ፡ እንግዳ ነገር ነበር። እኔ እስከማስታውሰው ድረስ አንዳቸውም ቢሆኑ፡ መቼም ቢሆን ማንም ሰው ማስታወስ ከቻለ፡ እሱ እውነት ካልሆነ በስተቀር ሌላ ነገር ተናግሮ አያውቅም። ሁሉም ነገር እሱ በተናገረው መሠረት ይፈጸማል።

10 በቅዱሳት መጻሕፍት መሰረትም፡ በዚህ የመጨረሻ ዘመን፡ ወደ እኛ ይመለሳል፡ ተብሎ ይጠበቃል። ይህ የሚሆነው ከመንፈስ ጥምቀት፡ በልሳኖች መናገር፡ መለኮታዊ ፈውስና፡ የመሳሰሉት ነገሮች፡ ከሆኑ በኋላ ነው። የጴንጤቆስጤ መልእክት ማጠናቀቂያ ዛሬ የምንናገረው ነገር ነው። ይህ የክርስቶስ አገልግሎት እርሱ በምድር ላይ በነበረበት ጊዜ ያደረጋቸውን ተመሳሳይ ነገሮች፡ በመጠቀም በሕዝቡ መካከል ራሱን የሚያስመስልበት ነው፣ የእርሱ አካል የሆነችው፡ ሙሽራው፡ የጋብቻ ሥነ ሥርዓቱ፡ ከመፈጸሙ በፊት፡ ልክ እንደ ባል እና ሚስት፡ ወይም እንደ ንጉሥ እና ንግሥት፡ ተመሳሳይ ነገሮችን እያደረገች ነው።

11 በዚህ ሳምንት፡ እግዚአብሔር ቢፈቅድ፡ በዘመቻችን እዚህ፡ በኤምባሲ ሆቴል፡ በ—በዚያ ላይ የተወሰነውን ለመናገር፡ ትሑት በሆነው መንገድ ለመተዋወቅ እፈልጋለሁ። የምንኖርበት ጊዜና ሰዓት፡ አንድ ሰው የትኛውን መንገድ መሄድ እንዳለበት፡ ምን ማድረግ እንዳለበት ወይም እንዴት መዞር እንዳለበት ካላወቀ፡ ከእንግዲህ—በእምነት እየሄደ አይደለም፡ በግምት፡ በድፍረት እየተጓዘ ነው። **በድፍረት ማድረግ** ማ—ማለት "ህጋዊ ባልሆነ መንገድ ሥልጣን ለመቀጠል መሞከር ማለት ነው።" ስለዚህ እግዚአብሔር

በዚህ ሰዓት እንደሚሆን የተናገረውን ነገር ለማወቅ ትክክለኛውን፡ ህጋዊ ሥልጣን ካላገኘን እንዴት ይህንን ሰዓት እንጋፈጣለን? በቃሉ በማመን፡ አሁን እየሆኑ ያሉትን፡ ነገሮችና፡ የሕዝቡን ሁኔታ፡ የሰዎችን ሁኔታ፡ የቤተክርስቲያንን ሁኔታና፡ የመሳሰሉትን በማወቅ፡ መጋፈጥ አለብን።

12 ይህን ማወቅ አለብን፡ ከዚያም እንዴት ልንጋፈጠው እንደምንችል ማወቅ አለብን። በዘፈቀደ፡ ብለን፡ እንደምንጠራው፡ ያንን እንዴት ማድረግ እንደሚቻል ካ—ካላወቃችሁ፡ እዚህ እንደሚሆን ተሰፋ በማድረግ፡ **ይህን** ተሰፋ በማድረግና **ያንን** ተሰፋ በማድረግ፡ "ይህ ይሆን?" እያላችሁ በሁሉም ዘላችሁ ትገባላችሁ፡ እግዚአብሔር ግን እንዲህ እንድናደርግ አይፈልግም። እርሱ ስለዚህ ዘመን የተናገረውን እንድናውቅ፡ ከዚያም በእምነት እንድንገናኘው ይፈልጋል፡ ምክንያቱም እንዲህ እንደሚሆን ተናግሯል። ስለዚህ—እውነተኛ እንደሆናችሁ እናውቃለን፡ ምክንያቱም ይህን ለማድረግ የሰው ቃል አልሰማችሁም፡ ምን ማድረግ እንዳለብን የሚነግረን ቃሉን አግኝተናል። የሰማይ አባታችን በዚህ ሳምንት ይህንን ይሰጠናል ብ—ብለን ተሰፋ እናደርጋለን።

13 አሁን፡ ደግሞ ከጥቂት ደቂቃዎች በፊት፡ ወደ ቱክሰን ስለመምጣቴ የምናገረውን በማቋረጤ፡ ይቅርታ እጠይቃለሁ። እኔም ራሴ፡ ይህ የሕይወቴ ፍጻሜ ነው፡ ብዬ አስብኩ። የዚያን ቀን ጠዋት አሥር ሰዓት ገደማ በቤት ውስጥ በዚያ ራእይ ውስጥ የሆነውን የዚያ ሁኔታ አስደንጋጭ ሁኔታ፡ ማንም ሊቋቋም አይችልም ብዬ አሰቤ ነበር፡ ከዚያ በኋላ በሕይወት ለመኖር የሚችል ማንም የለም ብዬ አሰብኩ። ምክንያቱም፡ ከሞትኩ በኋላ ባለቤቴና ልጆቼ ከእርሱ ጋር እንዲሄዱ ከ—ከልጄ ጋር ዝግጅት በማድረግ፡ ወደ ቱክሰን መጣሁ፡ ምክንያቱም መጨረሻዬ ይህ ነው ብዬ አሰቤ ነበር። እኔም፡ በፎኒክስ ይህ ከመሆኑ በፊት፡ በብዙ ስብሰባዎች ላይ እንዴት እንደሚሆን ነግሬያችኋለሁ።

14 እና፡ ከጥቂት ወራት በኋላ፡ አንድ ቀን ጠዋት ከቱክሰን በሰተ ሰሜን በሚገኘው፡ ሳቢኖ ካንየን ውስጥ ነበርኩ። እዚያ ላይ እየጸለይኩ ነበር። እየጸለይኩ ሳለው፡ እጄን ወደ ላይ አንሥቼ፡ እንዲህ አልኩ፡ "አባቴ ሆይ፡ እንደምንም እንድትረዳኝ እለምንሃለሁ፡ አሁን እያጋጠመኝ ላለው ዘመን፡ ጥንካሬን ስጠኝ። ሥራዬም በምድር ከተፈጸመ፡ ወደ አንተ እመጣለሁ። ወደዚህ በመምጣቴም አልቆጭም፡ ነገር ግን ቤተሰቦቼን እንደምትንከባከብ አውቃለሁ። ለዚህም ሰዓት ጥንካሬን እ—እጠይቃለሁ" አልኩ። አንድ ነገር እጄን መታኝ!

15 አሁን፡ ለሬዲዮ አድማጮች፡ የተናገርኩት ነገር እንግዳ ሊመስል ይችላል፡ ግን እውነት ነው። እግዚአብሔርም ፈራጁ ነው።

16 በእጄ ውስጥ ተመለከትኩ፡ አንድ ሰይፍ ነበር፡ እጀታው ላይ ሰገባ ነበረው። መያዣው እራሱ ከዕንቁ የተሠራ ነበር፡ ልክ መያዣው ክፍል ላይ እንደ-ወርቅ ዓይነት መያዣ ነበረው። ስለቱ ራሱ የ—የሚያንጸባርቅ ይመስል ነበር፡ ኦህ፡ ልክ የጸዳ ወይም በፀሐይ እንደሚያብረቀርቅ ነገር ነበር።

17 አሁን፡ ተራራ እናት ላይ፡ ጠዋት አሥር ወይም አሥራ አንድ ሰዓት ገደማ ነበር። ሰው ብቻውን ሆኖ (በጥሩ አእምሮዬ እንደሆንኩ ይሰማኛል) ከየት እንደሆነ ያማይታወቅ ሰይፍ ይዞ አሰቡት፡ ከሰዎች በማይሎች እና ማይሎች

ርቃችሁ፡ እዚያ መቆም ምን እንደሚሰማችሁ መገመት ትችላላችሁ። ወሰድኩና፡ ወደ ኋላ እና ወደፊት ሰይፉን ሲወዛወዝ፡ ተሰማኝ፡ እና፡ ስለምን፡ ሰይፍ ስለሆነ።

18 ዙሪያውን ቃኘሁ። አልኩኝም፡ “ይህ፡ አሁን፡ እንዴት እንዲህ ሊሆን ቻለ? እዚህ ላይ ቆሜያለሁ፡ በትክክል፡ እዚህ፡ በዙሪያዬ በማይሎችና ማይሎች ርቀት ሰው አልነበረም፡ ታዲያ ያ ከየት መጣ? እኔም እንዲህ አልኩኝ፡ “መልካም፡ ም—ምናልባት መጨረሻዬ ደርሷል እያለ ያለው—ጌታ ነው።”

አንድ ድምፅም፡ “ይህ የእግዚአብሔር ሰይፍ ነው፡” ሲል ተናገረ።

19 እንዲህ ብዬ አሰብኩ፡ “እሺ፡ ሰይፍ፡ እ... እንደ ንጉሥ፡ እንደ ወታደር፡” በእንግሊዝ እና በተለያዩ ቦታዎች ያደርጉት እንደነበረ፡ ታውቃላችሁ። “ያ፡ ለጀብደኛ ነው፡” ብዬ አሰብኩ። እንዲህ አሰብኩ፡ “መልካም፡ ምናልባት እጄን በሰዎች ላይ መጫን ይኖርብኝ ይሆን፡ ወይም... ” ታውቃላችሁ፡ የ... የሰዎች አእምሮ በቀላሉ ሊረበሽ ይችላል። አትረዱትም። አዕምሯችን ውሰን ነው፣ የእሱ ግን ገደብ የለሽ ነው። ስለዚህ፡ እዚያው እንደነበርኩ፡ ከ... ከዚያም እጄን ትቶ ሄደ የት እንደሄደ አላውቅም፡ በቃ ጠፋ። ለምን፡ አንድ ሰው ስለመንፈሳዊ ነገሮች ትንሽም ቢሆን ካልተረዳ፡ እ—እንደዚህ ዓይነት እብደት ያጋጥመዋል። እዚያ ብትቆሙ ኖሮ፡ ምን እንደሆነ ትገረሙ ነበር።

20 እርሱም እንዲህ አለ፡ “ራእዩ ሰለ አንተ መጨረሻ አይደለም። ለአገልግሎትህ ነው። ያ ሰይፍ ቃሉ ነው። ሰባቱ ማህተሞች ይከፈታሉ፡ ሚስጥሮች... ”

21 ከዚያ ከሁለት ሳምንታት፡ ወይም፡ ከሁለት ወራት በኋላ፡ ከዚያ በኋላ፡ ያ ሲሆን በተራራው ላይ ከብዙ ከጓደኞቼ ጋር ነበርኩ። ሰባቱ መላእክት፡ ልክ እናንተ ቆማችሁ እንደማያችሁ ሁሉ፡ ከሰማይ እየበረሩ ወረዱ። በተራሮቹ ውስጥ ያሉት ድንጋዮች እየተነሱ ወደ ታች ተንከባለሉ፡ እ—እዚያ የቆሙ ሰዎች እየጮኹና እየሮጡ ነበር፡ ታውቃላችሁ፡ አቧራ በሁሉም ቦታ እየበረረ ነበር። ይህ በሆነ ጊዜ፡ እርሱም፡ “ወደ ቤትህ ተመለስ። አሁን፡ እያንዳንዱ መልአክ የሰባቱ ማህተሞች አንድ አንድ ማሕተም ይሆናሉ” አለኝ።

22 ይህም፡ በቴፕ ላይ ይገኛል። መጽሐፉም በቅርቡ ይወጣል፡ ሰዋሰው እንደገና እየታዬ ነው። አሁን እንደምታውቁት፡ የእኔ ሰዋሰው በጣም ጥሩ አይደለም፡ ሰዎች አይ... የምትወዱኝና የእኔን ሰዋሰው እንዴት መረዳት እንዳለባችሁ የምታውቁ ሰዎች መሆን አለባችሁ። ነገር ግን አንዳንድ የሥነ መለኮት ሊቃውንት የእኔን ሰዋሰው እ—እያስተካከሉልኝ ነው፡ መ... መልካም፡ ምናልባት እዚያ ላይ የተሳሳተ ቃል ተናግሬ ይሆናል። ምንም እንኳን አላውቅም። ስለዚህ፡ አንድ ሰው ሲስቅ ሰምቻለሁ፡ ስለዚህ “የቃላት አጠራሬ” ትክክል አልነበረም ብዬ እገምታለሁ። ነገር ግን ልክ እንደ ደችማን፡ ምናልባት፡ የምለውን ሳይሆን ምን ለማለት እንደፈለኩ ውሰዱ።

23 በፕሮግራሙን ለመጨረስ፡ ሦስት ደቂቃዎች ብቻ እንደቀሩ፡ ተነግሮኛል።

24 አሁን፡ እናንተ በሬዲዮ የምትከታተሉን ውድ ወገኖቼ፡ እንዲሁም እናንተ ታዳሚዎች ሆናችሁ የታመማችሁና የተቸገራችሁ፡ ለታመሙ ሰዎች ስንጸልይላቸው እጆቻችሁን እርስ በርሳችሁ ትጭናላችሁ። አሁን፡ ኢየሱስ ለቤተክርስቲያኑ የሰጠው የመጨረሻ ተልዕኮ፡ “እነዚህ ምልክቶች

የሚያምኑትን ይከተላሉ።” “እነርሱ፥” እነርሱ የሚያምኑ! “በታመሙ ላይ እጃቸውን ቢጭኑ፥ ይፈወሳሉ።”

25 የሰማይ አባት ሆይ፥ ዛሬ እንደ ልጆችህ ነን፥ ያዘዝከንን እንፈጽማለን። በእነዚህ ሁሉ የሰልክ ጥያቄዎች ላይ እጃችንን እንጭናለን። በሬድዬ ስርጭት ያሉት ሁሉ፥ እንዴት እንደተቸገሩ፥ ሰቃያቸውን ታያለህ። እዚህ ያሉትን የተቸገሩትን፥ እየተሰቃዩ ያሉትን ታያቸዋለህ። አምላክ ሆይ፥ በተናገርከው ቃል ላይ በማመን፥ ለአንተ አሳልፈን እንሰጣቸዋለን፥ “እነዚህ ምልክቶች የሚያምኑትን ይከተላሉ። እጃቸውን በበሽተኞች ላይ ቢጭኑ፥ ይፈወሳሉ።” ጌታ ሆይ፥ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም፥ አድረገው። አሜን። [በቴፕ ላይ ባዶ ቦታ አለ—አርታዒ።]

[ወንድም ብራንሃም የመጀመሪያውን የሬዲዮ ስርጭት አበቃ—አርታዒ።]

☆ ☆ ☆ ☆ ☆ ☆ ☆

26 አመሰግናለሁ፥ ወንድም ሻካሪያን። በርግጥም ወደ ሰርጭቱ መመለስ፥ በሬዲዮ ዓለም ከሚገኙ ጓደኞቻችን ጋር መነጋገር፥ እንዲሁም እዚህ መገኘት ትልቅ እድል ነው።

27 ነገ ከሰዓት በኋላ ወደ ኤምባሲ ሆቴል መጥታችሁ፥ ጸሎት እንዲደረግላችሁ፥ ጥሪውን እናስተላልፋለን። ከዚህም በላይ፥ ኃጢአተኞችንና ባክ ያደርጉትን አምጧቸው። ለታመሙ ሰዎች ከጸለይን፥ እግዚአብሔር ያለማቋረጥ ታላላቅ ተአምራትን ሲያደርግ እናያለን፥ ነገር ግን ያ በሁለተኛ ነው። ዋናው ነገር መዳን፥ በእግዚአብሔር መንፈስ መሞላት ነው፥ በጥቂት ደቂቃዎች ውስጥ ስለነሱ እነግራችኋለሁ፥ አስፈላጊነቱን እንዴት በእግዚአብሔር መንፈስ መሞላት እንዳለብን እነግራችኋለው።

28 መለኮታዊ ፈውስ ብዙውን ጊዜ የሰዎችን ትኩረት ይሰባልና፥ ሰዎችን ወደ እግዚአብሔር ፊት ያመጣቸዋል። እግዚአብሔር አ—አንድ ነገር ሲያደርግ-... መልካም፥ አይረዱትም። እንዴት እንደሚሠራ በሜካኒካዊ መንገድ ማሳየት አንችልም። እግዚአብሔር ይህን የሚያደርገው በራሱ መንገድ ነው። የሆነ ቦታ አንድ ኃይል መኖሩን ማወቅ፥ ከሰው ልጅ ግንዛቤ በላይ የሆነ ነገር ማድረግ እንደሚችል ማወቅ፥ ያ ደግሞ የሰዎችን ትኩረት ይሰባል፥ ወደ እግዚአብሔርም በግ እንዲመለከቱ ያደርጋቸዋል። ሁሌም፥ መለኮታዊ ፈውስ፥ እኔ እንደተነገረኝ፥ ራሴም፥ እንደማምነው፥ ከሰልሳ፥ ምናልባትም፥ ከሰባ በመቶ የሚሆነው፥ የጌታችን አገልግሎት፥ መለኮታዊ ፈውስ ላይ የተመሰረተ ነበር። ይህንንም ያደረገው ሕዝቡን ለመሳብ ነው። ከዚያም እዚያ በደረሱ ጊዜ፥ እንዲህ አለ፥ “እኔ እርሱ እንደ ሆንሁ ካላመናችሁ፥ በኃጢአታችሁ ትሞታላችሁ” አላቸው።

29 አሁን፥ መለኮታዊ ፈውስ ሰዎችን ወደ ጌታ ኢየሱስ እንዲመለከቱ ለማድረግ፥ ታላቅ መሳቢያ ነው። ዶክተር ኤፍ ኤፍ ቦስዋርዝ፥ እንደ ብዙዎቻችሁ፥ ጓደኛዬ ነበር፥ አውቀዋለሁ፥ እንደ ወጣት አገልጋይ አገልግሎቱ ለእኔ ትልቅ ትርጉም አለው። በሰብሰባዎቼ ላይ ጀመርኩና፥ ከዚያም ወንድም ቦስዋርዝ ጋር እሄድ ነበር። እንዲህ ይል ነበር፥ “መለኮታዊ ፈውስ፥” አሁን ትንሽ ሃሳብ እሰጣችኋለሁ፥ እርሱም፥ “መለኮታዊ ፈውስ የአሳ መንጠቆ ላይ ያለው ማጥመጃ ነው” ይለኝ ነበር። “ዓሳውን መንጠቆውን አታሳየውም፥” አለኝ። ማጥመጃውን ታሳየዋለህ፥ ከዚያም ማጥመጃውን አጥብቆ በመያዝ

መንጠቆውን ይይዛል።" ስለዚህ እኛ ለማድረግ የምንሞክረው ይህ ነው። ያ... ያ... ዓላማችን ሰዎችን ወደ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ማምጣት ነው። እርሱም ትናንትም፥ ዛሬም፥ ለዘላለም ያው ነው። ስለዚህ ቀደም ባሉት ጊዜያት ፈዋሽ ከነበረ፥ ዛሬም ፈዋሽ ነው።

30 በሬዲዮ ስርጭት ላሉት ለታመሙ ሰዎች ከመጸለዬ በፊት የግል ምስክርነት ብቻ ላቅርብ። ከጥቂት ቀናት በፊት፥ በአስራ አምስት ወይም በሃያ ወንድሞች ፊት ታላቅ ነገር የተፈጸመበት ተራራ ላይ ተቀምጬ ነበር፥ በዚያም የጌታ መልአክ ወረደ፥ ታላቅ ብርሃን እንደ ተወርዋሪው ኮከብ እየበረረ፥ በተራሮች መካከል እየፈነዳ፥ ድንጋዮች ሁለት መቶ ጫማ ያህል ተፈናጥሮ እየበረረ፥ ከዚያ በላይም፥ የዛፎችን ጫፍ፥ እየቈራረጠ ነበር። እኔም ከሱ በታች ቆሜ ነበር። ይህ ከመሆኑ ከጥቂት ወራት በፊት፥ ይህ እንደሚሆንና ምን እንደሚፈጠር ነግሬያቸው ነበር፥ በግልጽ ለመናገር፥ ከአንድ ቀን በፊት ተነግሯቸው ነበር። እነዚህ ሁሉ ሰዎች ለማምለጥ እየሞከሩ፥ ከጭነት መኪናዎች ስር ስሮጡና የቻሉትን ሁሉ ሲያደርጉ ነበር። ምን እንደሆነ አያውቁም ነበር። ተናገራቸው ከዚያ በኋላ ወዲያውኑ ምን እንደሚሆን ነገራቸው።

31 በዚያ በተገኘበት፥ በዚያው ድንጋይ ላይ ተቀምጦ፥ ከሜኔሶታ የ— የመጣው፥ አንድ ጓደኛዬ ከእኛ ጋር ነበር። የእርሱ ሰዎች በዚህ ጠዋት እዚህ ናቸውና እርግጠኛ አይደለሁም ነገር ግን እርሱ እዚህ በሌሎች ክፍሎች ሊኖር ይችላል። ዶናሾን ዌርትስ የተባለ፥ ጥሩ ወጣት ነው፥ የሉተራን እምነት ተከታይ የነበረ ሲሆን ሕይወቱን ለክርስቶስ የሰጠና በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ ሰው ነው። ዕድሜው ወደ ሠላሳ የሚጠጋ፥ ቤተሰብ ያለው፥ ሁለት ወይም ሦስት ትናንሽ ልጆች ያሉት፥ በጣም ትሑት የሆነ የጀርመን ልጅ ነው። ሦስት ወይም አራት መቶ ጎረቤቶች ለመሆን ወደ ገቡበት ቦታ፥ ከእኔ ጋር ጎረቤት ለመሆን ወደ ቱክሰን ወረደ። ስለዚህ እሱ...

32 እንዲህ ያሉ ጐረቤቶች በማግኘቴም ደስተኛ ነኝ። ከደቡብ አፍሪካ፥ ከሁሉም ቦታ፥ አጠገበ ለመሆን ብቻ፥ ይ... ይከተሉኛል፥ እነሱም ከእኔ ጋር ለመቀራረብና አብረውኝ ለመኖር እንዲሁም በጌታ ደስታ ለመደሰት ሲሉ ነው።

እንዲህ ዓይነቱ ትሑት ሰው፥ ብዙም አስተውየው አላውቅም።

33 እርግጥ ነው፥ የማውቃቸውና ከእኔ ጋር ህብረት ያሚያደርጉ ሰዎች ልክ እንደ ወንድሜና፥ እኅቴም ናቸው። ማን እንደሆነ፥ እመለከታቸዋለሁና፥ ከመሰመር እየወጡ እንደህነ ካሰብኩ፥ ወደ አንድ ጐን ወሰጄ እናገራቸዋለሁ፥ ምክንያቱም እወዳቸዋለሁ። አብረን በክብር መኖር እንፈልጋለን። አንዳንድ ጊዜ፥ ሰብሰባዎች ውስጥ፥ ከባድ ነገር የሚናገራችሁ ይመስላቸዋል። እንደዛ አይደለም... ስለማልወዳችሁ አይደለም፥ ግን ከ—ከ... ከልቤ የመጣ ነው፥ ምክንያቱም አንድ መንገድ ብቻ መሆን አለበት። እግዚአብሔርን ማገልገል የሚቻልበት አንድ መንገድ ብቻ ነው፥ ሀ... ሀሳባችን ምንም ይሁን ምን፥ በመንገዱ መቆየት አለብን። መንገዱ!

34 ዶናሾን፥ በጆሮው ቀኝ ጫፍ ላይ፥ የጆሮውን መጠን በሦስት እጥፍ ያህል ያበጠና፥ በጣም ቀይ ሆኖ አየሁ። ደኅና፥ አሁን እያሰብኩ ምናልባት፥ እዚያ በረሃ ውስጥ ለጥቂት ቀናት፥ በነበረንበት ቦታ፥ ምናልባት ጆሮውን እሾኽ ነግር ወግቶት ሊሆን ይችላል ብዬ አሰብኩ። ነገር ግን፥ እጁን በመያዝ፥ ካንሰር መሆኑን

አወቅኩ። ስለዚህ ለዶናቮን፡ እንዲህ አልኩት፡ “ዶናቮን፡ ይህ... ከስንት ጊዜ ወዲህ ነው በጆሮህ ላይ የቆየው? ” እንደማያውቅ ሰው ሆኜ፡ ጠየኩት። እንዲህ አልኩት፡ “ዶናቮን፡ ይህ ምን ያህል ጊዜ ቆዬ? ”

እርሱም፡ “ወንድም ብራንሃም፡ ስድስት ወር ገደማ፡” አለኝ።

“ይህን ለምን አልነገርከኝም? ” አልኩት፡

35 እንዲህ አለ፡ “ኦህ፡ በጣም ሥራ ላይ እንደሆንክ ሰመለከት፡” እንዲህ አለ፡ “መናገር አ—አልፈለግሁም።” “አንድ ቀን ጌታ ሊነግርህ ይችላል ብዬ አሰብኩ፡” አለኝ።

እኔም፡ “ምን እንደሆነ አውቀሃል? ” አልኩት

እርሱም፡ “ጥሩ ግምት” አለኝ አለ።

እኔም፡ “ትክክል ነው” አልኩት።

36 በሁለተኛው ቀን፡ ጠዋት ልጁን እጁን ይዞ ሲወጣ፡ ምንም አልነበረውም፡ በነጋታው፡ በጆሮው ላይ ጠባሳ እንኳ አልነበረውም። ሙሉ በሙሉ ጠፋ።

37 ብዙ ጊዜ እንጫናለን፡ **ወደዚህ፡ ወደዚያ** ለመድረስ እየሞከርን ነው። ወይም... እያችሁ፡ ያ ነው፡ “ያመኑትን እነዚህ ምልክቶች ይከተላሉ።” “ለታመሙ ሰዎች ቢጸልዩ” አላለም። “በታመሙ ሰዎች ላይ እጃቸውን ቢጭኑ፡ ይፈወሳሉ!” በምናደርገው ነገር፡ በራሳችን ላይ፡ እምነት ሊኖረን ይገባል። መልካም።

38 ስለዚህ አሁን ዶናቮን እዚህ ሳይሆን አይቀርም። ታገኙታላችሁ። እዚህ ይሆናል፡ በዚህ ጠዋት እዚህ ካልሆነ፡ በሌሎች ክፍሎች ይገኛል። ታገኙታላችሁ፡ ምስክርነቱን ያውቃል።

39 ከዚህ በላይ ምን ማለት እችላለሁ? ሉቃስ፡ ወይም ዮሐንስ፡ አንዱ፡ ዓለም መቋቋም እንደማይችል ተናግሯል-... ብዬ አምናለሁ። በዚህ በመጨረሻው ዘመን በሰዎች መካከል ሰላደረገው ነገር የሚጻፉትን መጻሕፍት ይዘዋል፣ በሽተኞች እንዴት እንደተፈወሱ፡ የአልኮል ሱሰኞች እንዴት እንደዳኑ፡ በሺዎች የሚቈጠሩ፡ ከሁሉም ዓይነት በሽታዎች መከራዎች እንዴት እንደወጡ።

40 አሁን፡ በሬዲዮ ስርጭት፡ እንዲሁም እዚህ ያላችሁ፡ ዛሬ ጥዋት በሰልክ የገቡትን እጅግ በጣም ብዙ ጥያቄዎችን አሁን እዚህ ይዣለሁ፡ እዚህ ከደረሰንበት ጊዜ አንሥቶ ያለማቋረጥ እየደወሉ ነው። እዚህ ከገባን ጀምሮ፡ በሰልክ፡ አ... አንድ መቶ ዘጠና-ስድስት ጥያቄዎች በዚህ ጠዋት መጥቷል። ስለዚህ አሁን በጸሎት እንያያዝ። አማኞች ከሆናችሁ፡ በምድሪቱ ውስጥ፡ የትም ብትሆኑ፡ እጆቻችሁን እርስ በእርሳችሁ ላይ አድርጉ። ካልሆነ፡ እዚህም እዚያም እየጸለይን፡ እጃችሁን በመጽሐፍ ቅዱስ ወይም በሌላ ነገር ላይ አድርጉ።

41 የሰማይ አባት ሆይ፡ የዶናቮን ዌርትስ ትንሽ ምስክርነት፡ ጌታ ሆይ፡ በሺዎች ከሚቈጠሩ መካከል አንዱ ብቻ ነው፡ አንተ በጸጋህ... እዚህም ሆነ በሬዲዮ ስርጭት ያሉትን ሰዎች ልብ እንድትመለከት እጸልያለሁ። እነርሱም፡ እያንዳንዳቸው፡ ይፈወሱ። ክፉው ይተዋቸው፡ ከችግራቸውም ሁሉ ነጻ ይውጡ። አባት ሆይ፡ አድረገው። በልጅህ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ሰም፡ እንጠይቃለን። አሜን።

ጌታ ሆይ፡ አመሰግንሃለሁ... [በቴፕ ላይ ባዶ ቦታ አለ—
አርታዒ።]

[ወንድም ብራንሃም ሁለተኛውን የሬዲዮ ስርጭት አበቃ።—አርታዒ።]

☆ ☆ ☆ ☆ ☆ ☆ ☆

42 እና፡ ዛሬ ጠዋት እዚህ መሆን ለእኔ ሦስተኛ ጊዜዬ ነው። ማይ! ታውቃላችሁ፡ ህንፃውን በአስራ ሁለት፡ በአስራ አራት ደቂቃ፡ ወይም በሌላ፡ መልቀቅ እንዳለብን ተነግሮናል። አስተዳደሩ፡ በዚያ ሌላ ፎቅ ላይ ያለው፡ ማንኛውም አይነት ምግብ ማቅረብ እንደማይችሉ ተናግረዋል። ምግባችን ተራዝሟል። ታውቃላችሁ፡ ብዙ ኮርሶች አሉን። ዛሬ ጠዋት እዚህ ከእነዚህ ጥሩ ወንዶች ጋር፡ እኔ እንደምጠራው፡ ይህን ታላቅ መንፈሳዊ፡ የኢዮቤልዩ መልካም ምግብ በማግኘታችን፡ በጣም ደስ ብሎናል።

43 ነገ ከ—ከሰዓት በኋላ፡ በኤምባሲው ውስጥ የ... የሚደረገው አገልግሎት፡ እንደገና መጥቀስ እፈልጋለሁ። አሁን፡ እዚያ ላሉት ለታመሙ ሰዎች እንጸልያለን፡ እግዚአብሔር ከእኛ ጋር እንደሚገናኝም እንጠብቃለን። ይህ ስብሰባ ስኬታማ እንዲሆን፡ (የቻልነውን ሁሉ) ለማድረግ፡ የበኩሌን አስተዋጽኦ ለማድረግ መጥቻለሁ። ስብሰባችን ስለሆነ አይደለም ስኬታማ ምሆነው፡ ነገር ግን ሰዎች ኢየሱስ ክርስቶስ የመቀበል ስኬት ነው። ያ ነው ስኬት። ማንኛውም ስብሰባ፡ ምንም ያህል እግዚአብሔርን ብናወድስ፡ ብዙ ታላላቅ ነገሮችን ሲያደርግ ብንመለከት፡ ብዙ ጊዜ በመንፈስ ሲናገር ብንሰማው፡ ወዘተ፣ አንድ ነገር ካልተከናወነ በስተቀር፡ አንዳንድ ነፍሳት ወደ መንግሥቱ እንዲገቡ ካልተደረገ አይጠቅምም!

44 ወንድም ሻካሪያን አሁን—አሁን ስለምንኖርበት ዘመን ምን እንደሚያስብ እውነተኛ ሃ—ሃሳብ ሰጠ። የምንኖረው በጨዋታው ማብቂያ ሰዓት እንደሆነ፡ በፍጹም ልቤ አምናለሁ፡ በ—በምሽት ጥላዎች ውስጥ ነው የምንኖረው። ፀሐይ በጣም ርቃለች። ነገሮች ዛሬ ባሉበት ሁኔታ ሲሆኑ ሰናይ፡ ለምን፡ ሌላ ትውልድ ምን እንደሚያመጣ መናገር ይከብዳል። ከጥቂት ቀናት በፊት... .

45 አንድ ነገር እንድነግራችሁ ፍቀዱልኝ። እኔ በምኖርበት፡ አሪዞና ውስጥ ባሉ ሁሉም ትምህርት ቤቶች ላይ፡ ጥናት አደረጉ። ልጆቹ ሳያውቁት፡ የአዕምሮ ምርመራ፡ አደረጉ። ገምቱ እስኪ? የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችንና—የሰዋሰው ትምህርት ቤቶችን ጨምሮ፡ ሰማንያ በመቶ የሚሆኑት ልጆች የአዕምሮ ችግር አለባቸው። ከእነዚህ ውስጥ ሰባ በመቶ የሚሆኑት የቴሌቪዥን ተመልካቾች ናቸው። እያችሁ፡ ክፉዎች፡ ሳናውቅ ወደ ውስጣችን ገቡና... ለምን እንደሚመጣ ራሳችሁን ትጠይቃላችሁ። የእግዚአብሔር ድምፅ በእሱ ላይ ሲጮኽ መስማት ትችላላችሁ፡ ግን አሁንም እራሳችንን—በእሱ ውስጥ ተጣብቀን እናገኛለን።

46 አንድ አስደንጋጭ ነገር ልንገራችሁ። እያችሁ፡ "'ጌታ ሆይ፡ ጌታ ሆይ፡' የሚለኝ ሁሉ አይገባም፡" ነገር ግን የአባቴን ፈቃድ፡ የሚያደርግ ብቻ ይገባል። የእርሱ ፈቃድ ቃሉ ነው። በስብሰባዎች ውስጥ፡ በጣም ሃይማኖታዊ ልንሆን እንችላለን፡ ታላቅ ጊዜ ልናሳልፍ፡ መጮኽ፡ መ... መዝለል፡ እኔ ተቺ መ—መሆን አልፈልግም። ነገር ግን ለ—ለእግዚአብሔር የማደርገው ግዴታ አለብኝ፡ ያም ግዴታ ሀቀኛ መሆን እና እሱ የሚፈልገውን መናገር

ነው። በካሊፎርኒያ ቆይታዬ በማምናቸው ጉዳዮች ላይ—በእርግጠኝነት ውስጥ አብረውኝ ለጸኑ ሁሉ አ—አመሰግናሁ። እምነቴ ካልተናገርኩ፡ ግብዝ ነኝ፡ ለእናንተም ቅን አይደለሁም። ለእናንተ ታማኝ መሆን ካልቻልኩ፡ ለእግዚአብሔር እንዴት ታማኝ እሆናለሁ? ምክንያቱም እናንተን እያችኋለውና እናገራችኋለው፡ እርግጥ ነው፡ ለእግዚአብሔርም ቅኖች እንሆናለን፡ ነገር ግን እርስ በርሳችን ጋር በጣም ቅን እና ታማኝ መሆን አለብን። በእርግጠኝነት የ—የምንኖረው፡ በጣም አስከፊ በሆነ ዘመን ውስጥ ነው። መቼም ይሁን ከቆማችሁ... ?

47 እስቲ ትንሽ ትንታኔ ልስጣችሁ። "'ጌታ ሆይ፡ ጌታ ሆይ፡' የሚለኝ ሁሉ ወደ መንግሥቱ አይገባም፡ ነገር ግን የአባቴን ፈቃድ፡ የሚያደርግ ብቻ ነው።" ኢየሱስ በምድር ላይ፡ "ሰው በእያንዳንዱ ቃል እንጂ፡ በእንጀራ ብቻ አይኖርም፡" ብሏል። እያንዳንዱ! አሁን እና ያኔ፡ የሚነገር ቃል ሳይሆን፡ ግን በእያንዳንዱ ቃል።

48 በእግዚአብሔር ቃል ዘንድ፡ ከእግዚአብሔር ትእዛዛት መካከል... አንዲት የእግዚአብሔርን ቃል አለማመን፡ ሞት፡ ኀዘንና፡ ሁሉንም ዓይነት ህመምና የልብ ሕመም አስከተለ፡ ከእግዚአብሔር ቃል፡ አንዲት ቃል አለማመን ነው! የሰው ዘር አንድን ቃል በተሳሳተ መንገድ ማመኑ፡ ወደ ሞት ከወሰደው፡ ባለማመኑ፡ "በእርግጥም፡" ልክ ነው። ነገር ግን እንደሚሆን ተናግሯል። ሰይጣንም፡ "በእርግጥ አይሆንም" አለ። ነገር ግን ሆነ።

49 ስለዚህ፡ እያንዳንዱን የእግዚአብሔር ቃል መጠበቅ አለብን። የሰው ልጅ እና ይህ ሁሉ መከራ እና ነገሮች በሰው ዘር ላይ የደረሱት፡ አንድን ቃል በተሳሳተ መንገድ በመተርጐም፡ ወ—ወይም በተሳሳተ መንገድ በማመን ከሆነ፡ እንዴት አንድ ቃል ባለመጠበቅ ወደ ኋላ እንመለሳለን፡ ይህ ሁሉ ዋጋ ካስከፈለ፡ የልጁን ሕይወት እንኳን ካስከፈለ እንዴት እንስታለን?

**... ብዙዎች ተጠርተዋል፡... ጥቂቶች ተመርጠዋል።**

**... ብዙዎች ተጠርተዋል፡... ጥቂቶች ተመርጠዋል።**

50 ከዚህ መልእክት መውሰድ አልችልም፡ ነገር ግን፡ ምክንያቱም ጊዜ የለንም፡ ነገር ግን ለእናንተ አንዳች ነገር ለመስጠት ነው።

51 እስቲ ይህን እናስብ... አንድ ቀን ከወንድም ሻካሪያን ጋር፡ ከብቶችን ወደሚያዳቅሉበት ቦታ ሄድኩ። ወንድም ሻካሪያን በ—በ... በወሰደኝ ላቦራቶሪ ውስጥ አይቻለሁ። እነሱም የወንድ በሬ የዘር ፈሳሽ፡ የክብሪት እንጨት በሚመስል፡ በትንሽ... መሳሪያ፡ ብዙ የዘር ፈሳሽ ወሰዱና፡ በመቶዎች በሚያጎላው መስታወት ስር አስቀመጡት። በዚያ ፈሳሽ ውስጥ፡ የሚዘሉ ትናንሽ ዘሮች ነበሩ። ዘር ከወንዱ፡ እንቁላልም፡ ከሴቷ እንደሚመጣ እናውቃለን። እዚያም የነበረውን፡ ኬሚስቱን ጠየኩት፡ "ያንን እንደዚህ የሚዘል ትንሽ ነገር ምንድነው? "

እርሱም፡ "ያ—ትንሽ ነገር ኮርማዎች እና ጥጆች ናቸው" አለኝ። አያችሁ?

እኔም ጠየቅኩት፡ "በዚያን ትንሿ ጠብታ? "

እርሱም፡ "አዎን" አለ።

52 እኔም፡ “እንደዛ ከሆነ ምናልባት በጠቅላላው ዘር ፈሳሽ ውስጥ አንድ ሚሊዮን የሚሆኑ ሊኖሩ ይችላሉ? ” አልኩት

እሱም፡ “ኦህ፡ አዎን” አለኝ። አያችሁ? አሁን፡ ተከታተሉኝ።

53 አሁን፡ ይህ ታላቅ ነገር በሚሆንበት ጊዜ፡ እንቁላሏ ከአንድ ሚሊዮን ዘር ውስጥ አንዱን እየጠበቀች ነው። የትኛው ዘር እንደሆነ፡ ወይም የትኛው እንቁላል እንደሆነ ማንም ሊናገር አይችልም። የተፈጥሮ ልደትን ብትመለከቱ፡ ከ—ከድንግል ልደት የበለጠ ሚስጥራዊ ነው። ምክንያቱም፡ በዚህ የዘር ፍሬ ውስጥ፡ አንዱ ለመኖር የትወሰነ ሲሆን፡ የተቀሩት ደግሞ ይሞታሉ። የሚገናኘው የመጀመሪያው አይደለም፥ ከእንቁላል ጋር አብሮ የሚመጣው የመጀመሪያው ነው። ምናልባት እንቁላል ከዘሩ ጀርባ ወይም ከዘሩ መሐል፡ ሊነሣ ይችላል፣ ዘሩ ተመሳሳይ ነገር ሊያደርግ ይችላል፡ እንዴ እንቁላል። ጀርሙ ወደ እንቁላል ውስጥ ይንሸራተታል፡ ትናንሽ ጅራቶች ይወድቃሉ፡ የጀርባም አጥንት መፈጠር ይጀምራል። በዚያ ሙሉ ጭነት ውስጥ አንድ ብቻ ነው፡ ከሚሊዮን፡ አንድ ብቻ፡ ይህን ለማድረግ ይሄዳል፣ ይህም ለሰው አንዳንድ ባልታወቀ ኃይል፡ ይወሰናል። ሆኖም ግን፡ ሁሉም፡ ተመሳሳይ ናቸው፡ እነዚህ ዘሮች ሁሉ ተመሳሳይ ናቸው። በእንስሳት ውስጥ ተመሳሳይ ነገር ነው። በሰው ውስጥም ተመሳሳይ ነገር ነው። ወንድ፡ ሴት ልጅ፡ ቀይ-ጸጉር፡ ጥቁር-ጸጉር፡ ወይም ሌላ እንደሚሆን ይወሰናል። የሚወሰነው በእግዚአብሔር ነው። ሁሉም በተፈጥሯቸው፡ አንድ አይነት ይመስላሉ፡ ነገር ግን እዚያ ውስጥ ለሕይወት የተሾመ አንድ አለ፥ አንድ ከሚሊዮን፡ ሁሉም ግን ይመሳሰላሉ።

54 እስራኤል ግብጽን ለቆ በወጣችበት ወቅት፡ ሁለት ሚሊዮን የሚጠጉ ሰዎች በተመሳሳይ ጊዜ ከግብፅ ወጥተዋል። እያንዳንዳቸው የነቢዩን መልእክት ሰምተዋል። እያንዳንዳቸው የእሳቱን ዓምድ አይተዋል። ሁሉም በሙሴ፡ በቀይ ባሕር ተጠመቁ። ሙሴ በመንፈስ ሲዘምር ሌሎች—በመንፈስ ጮኹ፡ ከበሮውን መቱ፡ ከባሕር ዳርቻው ላይ ከማሪያም ጋር፡ ሮጡ። ሁሉም፡ ከአንድ መንፈሳዊ ዓለት፡ ጠጥተዋል። እያንዳንዳቸው፡ በየምሽቱ ትኩስ መና፡ ይበላሉ። እያንዳንዳቸው! ነገር ግን ምድሪቱን የወረሱት ሁለት ብቻ ነበሩ፡ አንድ ከሚሊዮን።

55 ፈተናው ምን ነበር? ሁሉም ከአንድ ዓለት ይጠጣሉ፡ ሁሉም ዛሬ ጠዋት እንደምንበላው ተመሳሳይ መንፈሳዊ መና ይበላሉ፡ የቃሉ ፈተና ግን ማረጋገጫ ነው። ወደ ቃዴስ-በርኔያ በመጡ ጊዜ፡ ወደ ተስፋይቱ ምድር ለመሻገር ሲጀምሩ፡ በቃል ሳይፈተኑ ማለፍ አልቻሉም። ሌሎቹ—አሥር ሰዎች ተመልሰው መጡና፡ “ይሄን ማለፍ አንችልም! ሕዝቡ... እኛ ለእነሱ እንደ አንበጣ ነን፡ ታላላቅ በቅጥር የታጠሩ ናቸው ከተሞቻቸው። ተቃዋሚዎች በጣም ብዙ ናቸው” አሉ።

56 ኢያሱና ካሌብ ግን ሕዝቡን አረጋጉት። እነሱም፡ “በጣም ብዙ አቅም አለን” አሉ! ለምን? እግዚአብሔር፡ ቃል የተገባላቸውን ምድር፡ ለቀው ከመሄዳቸው በፊት፡ “ይህችን ምድር ለእናንተ ሰጥቻችኋለሁ። ሰጥቻችኋለሁ። የእናንተ ነው” አላቸው። ነገር ግን አንድ ሚሊዮን ውስጥ አንድ ነበር የገባው።

57 በዛሬው ጊዜ በዓለም ላይ ክርስቲያን ነን-የሚሉ አምስት መቶ ሚሊዮን የሚያህሉ ሰዎች ያሉ ሲሆን፡ በየቀኑ አንድ ትውልድ ይጠፋል። አሁንም፡ መነጠቅ ዛሬ ቢመጣ እና አምስት መቶ ሰዎች፡ በዓለም አቀፍ ደረጃ፡ በመነጠቅ ቢወሰዱስ? ስለነሱ መሄድ በጭራሽ አታውቁም ወይም በጋዜጣ ላይ እንኳን፡ አይታዩም። የጌታ መምጣት ሚስጥራዊ መምጣት ነው። እንደ ሌባ ይመጣል። ትንሽ ይሆናሉ፡ እንደ...

58 ልክ ደቀ መዛሙርቱ ኢየሱስን በጠየቁት ጊዜ እንደነበረው፡ "ታዲያ ጸሐፍት ኤልያስ አ—አስቀድሞ መምጣት አለበት የሚሉት ለምንድን ነው? "

እርሱም፡ "እርሱ አቀድሞ መጥቶአል፡ እናንተ ግን አላወቃችሁትም" አላቸው።

59 ሰዎች ምን እንዳደረጉ አስባችሁታውቃለህ? ኤ-... ኤልያስ ይ-... ይመጣል ብለው ማመናቸውን ቀጠሉ። በመካከላቸው ነበር፡ እነሱ ግን አላወቁትም።

60 የሰው ልጅ በሚመጣበት ጊዜም እንዲሁ ይሆናል! ስለ እርሱም ተመሳሳይ ነገር ያደርጋሉ። የእግዚአብሔር መንፈስ እዚህ አለ። መልካም፡ ታዲያ በሱ ምን እናድርግ? እያደግን ስንሄድ እድገት ሳናደርግ መናገና፡ መሰል ነገሮችን፡ መብላታችንን እንቀጥልን?

61 ረቨረንድ ፒትስ ከጥቂት ደቂቃዎች በፊት እንደተናገረው፡ አንድ ዘር፡ መሬት ውስጥ እንዴት እንደሚገባ አስተውላችሁ ታውቃላችሁ? ብዙ ዘሮች መሬት ውስጥ አሉ። እግዚአብሔር በውኃው ላይ ሲንቀሳቀስ፡ በብርሃን፡ ብርሃንም ሲመጣ፡ የመጀመሪያው የእግዚአብሔር መገኘት፡ የተነገረው ብርሃን በእግዚአብሔር ቃል መጣ። የእግዚአብሔር ቃል አሁንም ብርሃንን የሚያመጣ ብቸኛው ነገር ነው። ውኃውም ሲመለስ፡ ዘሩ ቀድሞውኑ በምድር ውስጥ ነበር፡ ብርሃኑ በውስጣቸው ከህይወት ዘር ጋር የቀሩትን ዘሮች ብቻ ያወጣል፡ አወጣ። እግዚአብሄር ፍጥረቱን ይፈጥራል።

62 አሁንም፡ መንፈስ ቅዱስ ሲሰጥ፡ በፋሲካ ጠዋት ሌላ ብርሃን ምድርን መታ። እግዚአብሔርም በቅድመ እውቀቱ እዚህ ምድር ላይ እንደሚሆኑ፡ ለሚያውቋቸው ዘሮች፡ ብርሃን ለማምጣት ተሰጥቷል። የመጀመሪያውን የተፈጥሮ ዘር እንዳወቀ፡ መንፈሳዊው ዘር የት እንዳለ ያውቃል። እግግዚአብሔር ምድርን ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ ህልውና ባመጣበት ጊዜ፡ ሰውነታችሁ እዚሁ ምድር ላይ ተኝቶ ነበር። እኛ የምድር አካል ነን። እዚያ ተኝተን ነበር። በቅድመ እውቀቱ አማካኝነት ማን እንደሚወደውና ማን እንደሚያገለግለው እንዲሁም፡ ማን እንደማያገለግለው በትክክል ያውቅ ነበር። ቅድመ እውቀቱ ይህን ይናገራል። ካሆነ ግን፡ እርሱ አምላክ አይደለም። ወሰን የሌለው አምላክ መሆን አይችልም። እርሱ ወሰን አልባ ከሆነ፡ ሁሉንም ነገር ያውቃል።

63 ስለዚህ፡ ሰዎች ስሕተት ሲፈጽሙ ታያላችሁ። በእሱ ይሰናከላሉ። ይሮጣሉ፡ **ይሄንን** እና **ያንን** ያሰባሉ፡ ግን በትክክል አይሠራም፡ እናያለን። ነገር ግን የእግዚአብሔርን ፍጹም ፈቃድ ፈልጐ ማግኘት፡ በእርሱ መቆም የሚቻልበት ትክክለኛ መንገድ አለ፡ እግዚአብሔር የጠራችሁ ለዚህ ነው።

64 ወንድም ጃክ ከጥቂት ደቂቃዎች በፊት እንደተናገረው—እዚህ ፐርሺንግ አደባባይ ላይ፡ ያሚያጋባ ነገር ነበር። አንዱ **በዚህ** መንገድ፡ አንዱ **በዚያ**

መንገድ፣ ስለ ሥነ መለኮት ምሁራን፡ እና ስለመሳሰሉት ያወራሉ፡ ስለ ሥነ መለኮት ማወቅ ከፈለጋችሁ፡ ወደዚያ ሂዱ።

65 ለንደን ውስጥ በሃይድ ፓርክ ውስጥ እንዳለው አይነት ይመስለኛል። እኔም እዚያ ነበርኩ፡ እያንዳንዱ ሰው የራሱን ሃሳብ አለው። በ—በባቢሎን ውስጥ የ-የዘመናችን የዓለም ስብሰብ ነው።

66 ነገር ግን ወንድም ፒትስ ዛሬ ጠዋት ለ—ለእኛ ያለውን አስደሳች መልእክት ሲያስተላልፍ አስተውላችኋል? ከፓርኩ መውጣት ሲጀምር፡ ትንሽ የፋሲካ አበባ አገኘ። "በዚህ ሁሉ ግራ በመጋባት ውስጥ፡" ወደ እኛ ሲያመጣ፡ "'አዎ' ወይም 'አይደለም' ለማለት ምንም መንገድ አልነበረውም። በዚህ ሁሉ ግራ በመጋባት ውስጥ፡ የእግዚአብሔር ሕይወት በውስጡ ያበራ ነበር።" እግዚአብሔር በዚያ እንዲኖር ስላዘዘው፡ በብርሃኑ በዚያ ነበር። በዚህ ሁሉ ግጭት መሐል፡ ማንም አላስተዋለውም። መንፈሳዊ ጥቅም እንዳለው አልተገነዘቡም።

67 በዛሬው ጊዜም ቢሆን በስብሰባዎቻችንና በቡድኖቻችን፡ በቤተ ክርስቲያናችን በሃይማኖታዊ ተቋሞቻችን፡ በመሳሰሉት መካከል ያለው ሁኔታ ተመሳሳይ ነው። አንዱ **በዚህ** መንገድ ይጎትታል፡ "ባፕቲስት መሆን አለብን፡ ወይም ፕሬስባይተሪያን መሆን አለብን፡ **ይህ፡ ያ፡** ወይም **ሌላ** መሆን አለብን።" በዚህ ሁሉ መሐል፡ እያደገ የመጣ አበባ አለ። ከሁላችን መካከል ያደገ፡ በመካከላችን የእግዚአብሔር ኃይል አለ። እስቲ ለጥቂት ደቂቃዎች፡ ቆም ብለን እንመልከተው፡ በዚህ ሳምንት እንመልከተው፡ ከፊት ለፊታችን ሲገለጥ እንየው። እግዚአብሔር ያደርገዋል ብለን እናምናለን። አታምኑም? [ጉባኤው፡ "አሜን" አለ።—አርታዒ።]

68 አሁን ወደ ታች መውረድ እንዳለብን እገነዘባለሁ። ስለዚህ እያንዳንዳችን፡ እንጸልይ።

69 አምላካችን ሆይ፡ በአንተ ፊት አንገቶቻችንን ዝቅ ስናደርግ፡ ለመጠየቅ ብቁ እንዳልሆንን ይሰማናል። ነገር ግን ወደ አንተ ብንመጣ፡ እንደማትተወን፡ ቃል ገብተሃል። አሁን የተደረጉት እነዚህ ተራ ንግግሮች፡ በምንም መንገድ ዶክትሪን መሆን አይደሉም፡ "አንድ ከሚሊዮን ውስጥ፡" ነገ ግን ለማስታወስ ብቻ ነው። አንተም እንዲህ ብለሃልና፡

> ... **ወደ ሕይወት የሚወስደው መንገድ** ግን፡ **ጠባብ መንገዱም** ቀጭን **ነው፡ የሚያገኙትም** ጥቂቶች **ናቸው።**
>
> **የተጠሩት ብዙዎች ናቸውና፡ የተመረጡት ግን ጥቂቶች ናቸው።**

70 ዘላለማዊ አባት ሆይ፡ በዚህ በሰብሰባ ሳምንት በመላው ከተማ፡ የወንጌል ብርሃን ላክ። በወንድና በሴት፡ የወንድ የዘር ፍሬ ውስጥ ለመለየት እንደመሞከር፡ በራስህ ታላቅ፡ በአስተዋይ ስጭነትህ ማንኛውም ዘር ካለ፡ ወደ ስብሰባው ይግባ። መንፈስ ቅዱስ ብርሃንን ይስጣቸው። ጊዜው ከምናስበው በላይ ዘግይቷል ብለን እናስባለን። እግዚአብሔር ሆይ፡ ወደዚህ ስንመጣ፡ ምናልባት እዚህ ሊደረግ የሚችል ነገር እንዳለ በማመን ብቻ፡ እንጸልያለን ያም ሰዎችን፡ ወ—ወይም የመጨረሻውን በግ ለመያዝ ይጠቅማል። በረቱን በጐች ሲሞሉ፡ እረኛው በሩን እንደሚዘጋ፡ እናውቃለን።

71 በኖኅ ዘመን እንደነበረው ሁሉ፡ የመጨረሻው የቤተሰብ አባል ሲገባ፡ እግዚአብሔርን በሩን ዘጋ። እነሱም በሩን ደበደቡትና ደበደቡት፡ ግን በጣም ዘግይተዋል። ውድ እግዚአብሔር ሆይ፡ ዕድሉን አግኝተው ነበር።

አንተም፡ “እኔ የበጎች በር ነኝ” አለ።

72 የግጥሙ መዝሙር እንዴት አስደናቂ ነው፡ “ዘጠና ዘጠኝ ለአንተ በቂ አይደሉም? ግን፡ አይ፡ አንድ ተጨማሪ ነበር” የሚለው መዝሙር። እሱ ትንሽ ጥቁር በግ ሊሆን ይችላል፡ ወይም ትንሽ ማንም ሊሆን ይችላል፡ ትንሽ እሷ ወይም እሱ ሊሆን ይችላል። የት እንዳሉ አናውቅም፡ ነገር ግን የመጨረሻው ሰው መግባት አለበት ከዚያም በሩ ይዘጋል። ሁሉንም ነገር የምታውቅ፡ አምላክ ሆይ፡ ዛሬ ጠዋት ህይወታችንን መርምር። የመጨረሻውንም እናገኝ ዘንድ፡ ወደምንሄድበት ሁሉ ላከን፡ ይህም በሩ ተዘግቶ እረኛውም ከበጎች ጋር አንድ ላይ ውስጥ እንዲሆን ነው። ይሁን፡ ጌታ ሆይ። ዛሬ ያ መግባት ያለበት፡ አንድ ሰው ካለ…

73 “አብ የሰጠኝ ሁሉ ወደ እኔ ይመጣል። አባቴ ካልሳበው በቀር፡ ማንም ሊመጣ አይችልም።”

74 በዚህ ጉባኤ ውስጥ፡ እዚህ ወይም ከታች፡ ወይም በየትኛውም ቦታ የሚገኝ አንድ ሰው፡ ይህ ሰዓት፡ ሊሆን እንደሚችል፡ ትንሽ ስሜት ከተሰማው መልሱ፡ “አዎ፡ ጌታ ሆይ፡ ያ ትንሽ ተቅበዝባዥ እኔ ነኝ፡ ተቅበዘበዝኩና፡ ሕይወቴን በሙሉ ተዋግቻለሁ። የ—የ—የመምጣት ግዴታ እንዳለብኝ ተሰምቶኝ ነበር፡ ዛሬ ግን ከሸንፈት ጐን ተሰቅያለሁ። ወደ ላይም ሆነ ወደ ታች መሄድ አልችልም። በምንም መንገድ መሄድ አልችልም” ይበሉ። ኦህ፡ ታላቁ እረኛ ይምጣ፡ በደግነት እጁን ዘርግቶ ያቺን በጥንቃቄ ያምጣ፡ በትከሻው ላይ ይጭናትና በጥንቃቄ መልሶ ያምጣ።

75 ጌታ ሆይ፡ የታመመ፡ በተመሳሳይ ሁኔታ ውስጥ ያለ፡ ምናልባት እዚህ ላይ አንድ ሰው ሊኖር ይችላል፡ ዶክተሩ፡ “ምንም ማድረግ አይቻልም” ያለው። እሱን ለማዳን ከፍተኛ ጥረት ቢያደርግም፡ ሊታደገው አልቻለም። ከአቅሙ በላይ ነው። ማድረግ የ—የሚችለው ምንም ነገር የለም። መድኃኒቱ ወይም ስለቱ ሊደርሰበት አይችልም። ነገር ግን፡ ጌታ ሆይ፡ ለታላቁ ክንድህ የሚርቀው ምንም ርቀት የለም፡ ቃልህም ክንድህ ነው። ስለዚህ፡ አምላካችን ሆይ፡ ዛሬ ጠዋት፡ ከአንተ ጋር እየተነጋገርን ሳለን፡ እጅህን ዘርግተህ፡ የታመሙትንና ራሳቸውን መርዳት የማይችሉትን፡ ከሳይንሳዊ ጉዳዮች ሁሉ ርቀው፡ ከሃኪም ርቀው፡ እንዲፈወሱ እንጸልያለን። አድርገው፡ ጌታ ሆይ።

76 ስለ ዳዊት ስናስብ፡ በጥቂት በጐች ላይ፡ ጥቂት በጐች ላይ ብቻ ኃላፊነት ተሰጠው። አንድ ቀን ድብ መጥቶ ያንን አንድ ታናሽ በግ ይዞ ወጣና፡ (ልክ ካንሰር ሰውነትን እንደሚበላ)፡ ወይም እንደ ግዙፍ አንበሳ፡ ሊበላው ነበር። ዳዊት ግን፡ የ—የጠመንጃ መሣሪያ፡ ወይም፡ የሰይፍ ባለሙያው አይደለም፡ ነገር ግን ወንጭፍ ብቻ ተጠቅሞ፡ በጉን ተከትሎ ይሄድ ነበር። ትንሹን በግ ሊገድለው የ—የፈለገውን አውሬ ሲያገኘውም፡ በወንጭፉ ይገድለው ነበር። ቀላል እና ትንሽ መሣሪያ፡ ከቆዳ እና ከገመድ የተሰራ ይዞ ይወጣ ነበር፡ በእሱ ላይ ግን እምነት ነበረው።

77 ጌታ ሆይ፡ በመካከላችን ታላላቅ ሊቃውንት የሉም። እኛ ቀለል ያሉ ጸሎታችንም ትንሽ የሆኑ ሰዎች ነን፡ ዛሬ ጠዋት ግን የአባታችን በጎች ተከትለን ወጣን። ሲጋራ ለማጨስ፡ ሰላም ለማግኘት በመሞከር፡ በመከራ፡ ጎዳናዎች ላይ በሚያሳዝን ሁኔታ የምትባዝን ሴት፥ ብርጭቆውን አትሽቶ ወደ ኋላ መመለስ የሞከረው፡ ጠላት አጥብቆት የያዘው ሰው፡ ትክክለኛውን ነገር ለማድረግ የሞከረው ልጅ ወይም ሴት ልጅ፡ ከስህተቱ ለመላቀቅ የሚያስችል ጥንካሬን ግን ማግኘት አልቻሉም፥ ዛሬ ጠዋት በጌታችን በኢየሱስ ስም፡ ያንን በግ ለመውሰድ እንመጣለን። ጠላትንም እንቃወማለን፡ ምክንያቱም ቀላል ነገር ነው፡ የጸሎት ወንጭፍ፡ ነገር ግን ይህን ሰው ወደ አባታችን መንጋ ለመመለስ እየመጣን ነው፡ ይህም በእጃችን ለተሰጡት ነገሮች መልስ ለመስጠት እንድንችል ነው። የእግዚአብሔር ኃይል አሁን በሕዝቡ ልብ ውስጥ ያለውን እምነትን ይንካ፡ ያ የጠፋ ነፍስ ዛሬ ጠዋት ተመልሶ ይምጣ። የዚህ ሕይወት ፈተናዎች ወደ ኋላ ይመልሱት፡ እንዲሄድ ይፍቀዱለት። እንዲሁም በጌታው ትከሻ ላይ ተጭኖ ዳግመኛ ወደ ደህንነቱ ሲመለስ፡ ራሱን በደኅንነት ውስጥ ያግኝ። በኢየሱስ ስም እንጠይቃለን። አሜን።

78 እግዚአብሔር ሁላችሁንም ይባርክ። ነገ እስክንገናኝ ድረስ፡ አገልግሎቱን ለወንድም ሻካሪያን እሰጠዋለሁ። [በቴፕ ላይ ባዶ ቦታ አለ—አርታዒ።]

[ወንድም ብራናም ሦስተኛውን ክፍል ጊዜ አበቃ—አርታዒ።]

☆ ☆ ☆ ☆ ☆ ☆ ☆

79 ይህ፡ አ—አንድ የተሳሳተ ነገር ልነግራችሁ… እዚህ ቆሚያለው ብዬ ለመናገር በእግዚአብሔር ፊትም ሆነ በአንተ ፊት የበለጠ ሞገስ እንዳገኘሁ፡ ታውቃላችሁ ብዬ ተሰፋ አደርጋለሁ። ባለፈው ቀን፡ ኀምሳ-ስድስተኛ የልደት ቀኔን አልፊያለው። ይህ የአንድ አዛውንት መልእክት አይደለም። ከልጅነቴ ጀምሮ ይህን አምናለሁ። ይህ እውነት ካልሆነ፡ እግዚአብሔር በምድር ላይ ካለው እጅግ ሞኝ ሰው እኔ ነኝ። ሕይወቴን በሙሉ ለዚህ ዓላማ ሰጥቻለሁ። ይህንንም በቅንነት መናገር እችላለሁ፡ አሥር ሺህ ሕይወት ቢኖረኝ፡ ኖሮ ሃሳቤን በጭራሽ አልለውጥም።

80 አሁን፡ ግን ፈውስ ለሁሉም ሰው ተደራሽ ነው። አስታውሱ፡ ፈውስ በውስጣችሁ ነው። እግዚአብሔር በገነት ውስጥ በተከለው ጊዜ መቢያፈሩ ዛፍ ውስጥ፡ በውስጡ ሊኖር የሚችለውን እያንዳንዱን የፍሬ ዛፍ አስቀመጠ። አያችሁ፡ የ… የኮክ ዛፍ ወይም የፖም ዛፍ፡ ወይም የፍራፍሬ ዛፍ፡ በምድር ውስጥ ያለውን ውኃ በመጠጣት፡ ማደግ አለበት። አሁን እያንዳንዳችሁ ራሳችሁን ለማዳን፡ በእናንተ ውስጥ እነዚያ አቅሞች አሏችሁ፡ በእግዚአብሔር፡ በመጠመቅ በክርስቶስ ውስጥ (በውሃ ጥምቀት ሳይሆን)፡ በመንፈስ ጥምቀት ተተክላችኋል። ወደ ክርስቶስ የመጣሁት በውኃ ጥምቀት አይደለም። በመንፈሳዊ ጥምቀት ነው!

81 እግዚአብሔር ቢፈቅድ፡ ነገ ከሰዓት በኋላ፡ በዚህ ጉዳይ ላይ፡ **እንዴት** እና **የትኛው** እውነተኛ አተገባበሩ እንደሆነ እናገራለሁ። ከሰዓት በኋላ የምናቀርበው ስለሆነ አገልግሎቶቻችሁን አያስተጓጉልም።

82 አሁን ተመልከቱ፡ እያንዳንዳችሁ እዚህ እንደ አማኞች ቆማችኋል፡ አያችሁ፡ በክርስቶስ የነበረው ሕይወት በእናንተ ውስጥ ነው። እሱ ይችላል፡ ማየት ብቻ

ከቻላችሁ!

83 ከዛ እንዳትደርሱ ማገድ፣ እንዳታዩት ማድረግ የዲያብሎስ ሥራ ነው። ያ፣ ዕውር እንዲትሆኑ ሊያደርጋችሁ ይችላል፣ አያችሁ፣ ከዚያ የት እንደምትሄዱ አታውቁም። ዓይነ ሰውር የሆነ ሰው የት እንደምሄድ ማወቅ አይችልም፣ ማየት ከሚችል ሰው መረዳትን መፈለግ አለበት። መረዳት እስክንችል ድረስ፣ አንድ ሰው እውነት ምን እንደሆነ ሊነግረን ይገባል።

84 ክርስቶስም ስለ እናንተ ሞቷል፣ እናንተም ከዓለም ወደ ክርስቶስ ተተክላችኋል። በመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት፣ የሚያስፈልጋችሁ ነገር ሁሉ በእናንተ ውስጥ ይገኛል። ትክክል አይደለም? አሁን ማድረግ ያለባችሁ ብቸኛው ነገር ከዛ መጠጣት መጀመር ነው።

85 ዛፉ ሲጠጣ ቅጠሎቹን ማውጣት፣ ቡቃያዎቹን ማውጣት፣ ፍሬዎቹን፣ በየዓመቱ ማፍራት ይጀምራል። ፍሬው መሬት ውስጥ አይደለም፥ ፍሬው በዕፅዋቱ ውስጥ ነው። ሰንቶች ይህን ተገንዝባችኋል፣ "አሜን" በሉ። [ጉባኤው፣ "አሜን" አለ።—አርታዒ።] ስለዚህ፣ አያችሁ፣ ፍሬው በዕፅዋቱ ውስጥ ነው፣ እያንዳንዱ እፅዋት ከምንጭ መጠጣት አለበት። ዝናቡ ወደ ታች ሲወርድ፣ ለዚያ ተክል፣ ለመጠጣት ሕይወት፣ ይሰጣል። እና፣ እየጠጣ ሲሄድ፣ ያድጋል።

86 ልክ እንደ ቤተክርስቲያን፣ በዚህ ዘመን ማበብ እንዳለባት፣ ሙሉ ቡቃያ እስኪሆን ድረስ እያደገ ነው።

87 እኛም፣ እየጠጣን ስንሄድ፣ እያደግን እንሄዳለን። ነገር ግን ተክሉ ለመጠጣት ፈቃደኛ ካልሆነ፣ ተክሉ ማደግ አይችልም። አሁን ይህን፣ በየግላችሁ ብቻ እመኑት!

88 እርግጥ ነው፣ በሰብሰባ ውስጥ፣ ጌታ እንዴት እንደሚያደርግ ታውቃላችሁ፣ ምን እንዳደረጋችሁና ምን ማድረግ እንደሌለባችሁና፣ የመሳሰሉትን፣ የተለያዩ ነገሮችን ያሳያል። ዛሬ ጠዋት መንፈስ ቅዱስ በእኛ ላይ ይወርዳል ብለን ተሰፋ አድርገን ነበር፣ እንደቆምን ይወርዳል ብለን። እኔ ግን መጠበቄን ቀጠልኩ።

89 እንደማስበው፣ የታችኛው ክፍል ከዚህ እንድንወጣ እንደሚፈልጉ ማሰብ አስፈሪ ነገር ነው፣ አያችሁ። ነገር ግን እንድንወጣ ይፈልጋሉ፥ አሁን ዘግይተናል።

90 ይህን ግን፣ በሙሉ ልባችሁ እመኑት። እባካችሁ። እ—እንዴ እውነተኛው ሰው፣ በፊታችሁ ሞገስ አግኝቼ ከሆነ፣ ይህን እመኑት። አሁን እጆቻችሁን እርስ በ—በርሳችሁ ላይ አድርጉ።

91 አሁን ተመልከቱ፣ አሁን፣ መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ አላለም፣ "እነዚህ ምልክቶች ዊሊያም ብራንሃምን ይከተላሉ" አላለም። "ኦራል ሮበርትስን ብቻ ይከተላል፣" አላለም። "ወንድም ኮፕ' ወይም "አንድ ሰው" እንደሚከተለው አልተናገረም።

92 "እነዚህ ምልክቶች ይከተሏቸዋል፣" እንደ ብዙ ቁጥር ያመለክታል፣ "ያመኑት። እጃቸውን በበሽተኞች ላይ ቢጭኑ፣ ይፈወሳሉ።" እጃችሁን በያዛችሁበት ሰው ላይ ሕይወትን የሚያመጣው፣ በእናንተ ውስጥ ያለው የእግዚአብሔር ኃይል ነው፣ ሕይወት-ሰጪ የሆነው የመንፈስ ቅዱስ ምንጭ ነው።

93 ውድ አምላክ ሆይ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም፡ በዚህ ወሳኝ የቤተ ክርስቲያን ሰአት… ያለምንምን ፍርሃት ይቁሙ፡ ክርስቶስን፡ ከሞት ያስነሣው ኃይልም፡ የወንገልን እውነት ህይወት ይሰጣቸው፡ የኢየሱስ ተልዕኮ ይህ ነበርና፡ ይህም “እጃቸውን በድውዮች ላይ ቢጭኑ፡ ይፈወሳሉ።” እያንዳንዱ የአጋንንት ኃይል፡ እያንዳንዱ በሽታ፡ እያንዳንዱ ደዌ፡ እያንዳንዱ መከራ፡ በሕዝቡ ላይ የደረሰው እያንዳንዱ አሰጨናቂ ነገር፡ አሁን በእምነት ይተወው። አማኞች እንደመሆናችን፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እንጠይቃለን። አሜን።

94 አሁን እንደሚያደርግ ካመናችሁ፡ እጆቻችሁን አንስታችሁ አመስግኑት።

95 እግዚአብሔር ሆይ፡ ይህ ልጅ ካልተፈወሰ፡ ይሞታል፡ ጌታ ሆይ። ይህንን ቋጠሮ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አገሰጻለው። ከዚህ ንፁህ ከሆነው ልጅ ይልቀቅ። ኣሜን።

እንግዲህ፡ ዶክተሮች ሞክረው፡ አልተሳካላቸውምና። እመን ብቻ።

65-0424 አንድ ከሚልዮን
ክሊፍቶንስ ካፊተርያ
ሎስ አንጀለስ, ካሊፎርኒያ ዩ.ኤስ.ኤ

AMHARIC

©2024 VGR, ALL RIGHTS RESERVED

VOICE OF GOD RECORDINGS
P.O. BOX 950, JEFFERSONVILLE, INDIANA 47131 U.S.A.
www.branham.org

## የቅጂ መብት ማሳሰብያ

ይህ መጽሐፍ የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል ይሰፋ ዘንድ፣ በቤት ለግል ጠቀሜታም ሆነ ለሌሎች ሰዎች ያለ ክፍያ ለማበርከት፣ በቤት ማተሚያን መጠቀም ይቻላል። ይህ መጽሐፍ ያለ ቮይስ ኦፍ ጋድ ሪከርዲንግስ በጽሑፍ የተደገፈ ህጋዊ ፈቃድ መሸጥም ሆነ፣ አብዝቶ ማተም፣ በዌብ ሳይት ላይ ማስቀመጥ፣ በማከማቻ ዘዴዎች ላይ ማስቀመጥ፣ ወደ ሌሎች ቋንቋዎች መተርጎምም ሆነ የድጋፍ ማሰባሰቢያ አድርጎ መጠቀም የተከለከለ ነው። ህጋዊ መብቱም ሁሉ የተጠበቀ ነው®።

ለተጨማሪ መረጃ ወይም ተጨማሪ ግብዓቶች ቢፈልጉ፣ እባኮትን ይህ አድራሻ ይጠቀሙ፡

Voice Of God Recordings

P.O. Box 950, Jeffersonville, Indiana 47131 U.S.A.

www.branham.org